# አረጋዊ ገብረዮሐንስ ማን ገደለው?

በአስራት አብርሃም

**በጊዜ ምንገባው**
**ማምሸቱን የተውነው**
**ሌባ ወይም ሰይጣን**
**አይደለም… የፈራነው**
**ፅልመት ተገን አርገው**
**ማጅራት የሚመቱ**
**ገዥዎች ስላሉ ነው፡፡**



ይህ ግጥም በአሁኑ ጊዜ በኢትዮጵያ ያሉ ተቀዋሚ ፖለቲከኞች ስጋት የሚያመላክት ነው፡፡ የገዥው ፓርቲ ባለስልጣናት ቀን ህዝቡ እያየ በተቀዋሚ ፓርቲ አባላት ላይ ሲብስባቸው ወይም ሲደነግጡ ካልሆነ በስተቀር ጥቃት ለማድረስ አይደፍሩም፡፡ ማታ በጭለማ ከሆነ ግን እንድትመታ ወይ ማጅራት መቺ ገዝተው፣ ወይም ከአሁን በፊት በሆነ ነገር የተጣላህን ሰው ፈልገው ፣ **"አይዞህ! እንደፈለክ አድርገው!"** ብለው ይልኩብሃል፡፡ ዕድለኛ ከሆንክ ተደብድበህ በህይወት ትተርፋለህ፡፡ እስካሁን አራት የአረና-መድረክ ተወዳዳሪዎች በዚሁ መልክ ከፍተኛ ድብደባ ደርሶባቸው ከሞት ብቻ ተርፈዋል። ድንገት ጎደሎ ቀን ከገጠመህ ደግሞ ሞትህ የግድ ይሆንና ልክ እንደ አረጋዊ ገብረዮሐንስ የሰላማዊ ትግል ሰማዕት ሆነህ ትሞታለህ፡፡

ለምሳሌ ከፍተኛ ድብደባ ከተፈፀመባቸው የዓረና-መድረክ ተወዳዳሪዎች፤ አቶ አያሌው በየነ የተባለ በወቅሮማራይ የምርጫ ክልል መድረክን ወክሎ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የሚወዳደር በወታደሮች ተቀጥቅጦ፣ ንብረቱንም ተቀምቷል፡፡

አቶ ስሙር አባዲ በቆላ ተምቤን በአግበ የምርጫ ክልል ለክልል ምክር ቤት የሚወዳደር ከገጠር የመጡት ዘመዶቹን ሸኝቶ ወደ ቤቱ ሲመለስ የፌደራልና የዓብይዓዲ ከተማ ፖሊሶች እንዳይሆን አድርገው ከደበደቡት በኋላ "ሞቷል" ብለው ጨለማ ላይ ጥለውት ሄዷል፡፡

አቶ አወል ኢብራሂም የተባለ የዓቢይ ዓዲ ምርጫ ክልል ተወዳዳሪ በመዝናኛ ቦታ እያለ የሰከሩ በሚመስሉ ሰዎች ተደብድቧል፡፡

መምህር ገብረፃዲቅ ደስታ የታባለ በሰንቃጣ የምርጫ ክልል የሚወዳደር ደግሞ አሁን በሚኖርበት በሽሬ ከተማ "አገር አማን ነው" ብሎ ወደ ቤቱ ሲገባ የባለቤቱ የቀድሞ "ጓደኛ" ከግብረ አበሮቹ ጋር በመሆን አድብቶ ደብድቦት ሂዷል፡፡ በእርግጥ አሁን ወደ ምርጫው ከገባን ጀምሮ እየደረሱብን ያሉትን ጥቃቶች ሁሉም እንዘርዝር ብንል የተነሳንበትን ሃሳብ ሳንገልፅ ጊዜው ያልቅብናል፡፡ በአጠቃላይ በአሁኑ ጊዜ ትግራይ ውስጥ የዓረና-መድረክ አባል ሆነህ መገኘት ለሁሉም ዓይነት ጥቃቶች የተጋለጥክ እንድትሆን ያደርገሃል፡፡ ላንተ የህግ ከለላ የሚሰጥህ

አካል ፈፅሞ አታገኝም፡፡ ወደ ፖሊስ ጣቢያ ሄደህ “ጥቃት ደረሰብኝ” ካልክ መሳቂያ ነው የምትሆነው፡፡ ለምሳሌ አቶ አወል ኢብራሂም ተደበደብኩ ብሎ ለፖሊስ ሲያመለክት የወንጀል መርማሪው ፖሊስ **“ይህ መንግስት ያንተ መንግስት አይደለም፡፡ ከፈለክ ለመራራ ጉዲና ሄደህ አመልክት”** ነው ያለው፡፡ አወይ ጉዳችን! እኛማ መንግስት አለን፤ በመጠኑም ቢሆን የህግ ልዕልና አለ ብለን ነው እንጂ እንዲህ በጫካ ስርዓት የምንተዳደር መሆናችን ብናውቅማ... መቼ እንዲህ ተዘፋዝፈን እንገኝ ነበር!

ወደ ተነሳንበት ርዕሰ ጉዳይ እንነሳና ለመሆኑ አረጋዊ ገብረዮንስ ማን ገደለው? ለምንስ ተገደለ? ከግድያው ጀርባ ያለውስ ዓላማ ምንድነው? የሚሉትን ጥያቄዎች ማንሳት ተገቢ ነው፡፡ በእርግጥ ለሁሉም በአረጋዊ ገብረዮሐንስ አሟሟት ዙሪያ ለሚነሱት ጥያቄዎች የሚሆን መልስ ለማግኘት አስቸጋሪ ነው፡፡ በሂደት ዘመንና ሁኔታዎች ሲመቻቹ ከቀጥተኛው ገዳዩ ጀምሮ እስከ ላይ እንዲገደል ትዕዛዝ እስከ አስተላለፋት የክልሉ ባለስልጣናት ድረስ ያለውን ሰንሰለት የሚጋለጥበት  ጊዜ ሩቅ አይሆንም፡፡

እዚህ ላይ እኔ ለመግለፅ የምሞክረው እስካሁን ድረስ የተገለጠው ሃቅና ግድያው የተፈፀመበትን ሁኔታ ወይም አፈፃፀሙን በተመለከተ የተወሰነውን ነው፡፡

በነገራችን ላይ ከአረጋዊ ጋር የቆዬ እውቂያ ነው ያለን ዓረና ከመፈጠሩ በፊት ልክ የዛሬ 5 ዓመት በ1997 ዓ.ም እሱ የንግዱን ስራ እያካሄደ ጎን ለጎን ይማር ስለነበረ ለተወሰነ ጊዜ መምህሩ ሆኜ ነው የተገናኘነው፡፡ በሽሬ ከተማ “ባድሜ ዘመናዊ የፀጉር ማስተካኪያ” የሚል ከፍቶ ነበር የሚሰራው፡፡ ከዚያ ወዲያው ወደ አድዋ መማህራን ኮሌጅ በመዛወሬ ተለያየን፡፡  ዕጣ ክፍላችን ሆኖ መሰል ሁለታችንም ከሁለት ዓመት በኋላ ሽሬ የዓረና አባላት ስብሰባ ህጂ እሱም አባል ሆኖ እዚያው እንደገና ተገናኘን፡፡

አረጋዊ ምንም ወጣት ቢሆን በሳል አስተሳሰብ የታደለ፣ በንግድ ስራ  ራሱን ችሎ የሚተዳደር ባለትዳርና የስድስት ልጆች አባት ነበር፡፡ ምንም እንኳ የብዙ ቤተሰብ ሓላፊነት ቢኖርበትም የዓረና አባል ከሆነበት ጊዜ ጀምሮ አያሌ እንቅስቃሴዎችን በማድርግ በምዕራብና በማዕከላዊ የትግራይ ዞኖች ያሉትን አባላት በማንቀሳቀስና በማስተባበር ፈፅሞ ታይቶ የማይታወቅ የአዳዲስ አባላትን ንቅናቄ መፍጠር ችሏል፡፡ከዚህም በአሻገር ድርጅቱ ያለበትን የገንዘብና የሰው ኃይል ውሱንነት ተገንዝቦ ማንንም ሳይጠብቅ የራሱን ገንዘብ፣ ጉልበትና ጊዜ ተጠቅሞ የተሰለፈለትን ዓላማ ግቡን እንዲመታ ብዙ ለፍቷል፡፡

የእሱ አርአያ በመከተል ብዙ ወጣቶች በድፍረት ድርጅቱን ተቀላቅለው በብዙ አከባቢዎች ዓረና በሁለት እግሩ እንዲቆም አስችለዋል፡፡ በዚህ ጥንካሬውና በአደረገው አስተዋፅኦ ነው በ”ነበለት” ምርጫ ክልል ለህዝብ ተወካዮች መድረከን ወክሎ እንዲወዳደር ታጭቶ የነበረው፡፡ ይህን ሁሉ ሲያደርግ ግን ከብዙ ውጣውረድና እንግልት ጋር ነበር፡፡ በየጊዜው በፀጥታ ኃይሎች እየተያዘ ለሰዓታት ያህል “ወረቀት በተንክ፤ ሰው አነጋገርክ” እየተባለ ታስረዋል፡፡ እኛ መቀሌ ላይ ስናመለክት ደግሞ ወዲያው ይለቀቅና እንደገና ደግሞ በሌላ ቦታ ይይዙታል፡፡ እንደገና አቤት

ብለን ይለቀቃል፡፡ እንደዚያ ነው አብዛኛው የእኛ እንቅስቃሴ! የተለመደ ነገር በመሆኑም ከዚያ የከፋ ህይወትን የሚጠይቅ ነገር እንዲህ በቀላሉ ያጋጥማል ብለን አብዛኞቻችን አላሰብንም፡፡
ከላይ ለመግለፅ እንደሞከርኩት አረጋዊ ላይ ይደርሱ የነበሩት ማስፈራሪያዎችና ዛቻዎች በሌሎች አባሎቻችንም ላይ ይደርሱ ስለነበረ ብዙም የተለየ ትኩረት አላደረግንበትም፡፡

የካቲት 23/2002 ዓ/ም ግን ከወደ ሽሬ የተሰማው መርዶ አእምሮን የሚያደነዝዝ ህሊናን የሚያስት ነበር፡፡አረጋዊ በጩቤ በአሰቃቂ ሁኔታ መገደሉን የሚገልፅ መርዶ፡፡ እኔ በወቅቱ አዲስ አበባ ላይ በአንድነት ቢሮ እያለሁ ነው የሰማሁት፡፡ እዚያ ለመቆየት የነበረኝን ፕረግራም ሰርዤ ወዲያው ነበር ወደ ትግራይ የተመለስኩት፡፡ አባቴ ድንገት መነሳቴ ገርሞት ሲጠይቀኝ ስጋት እንዳይገባው ብዬ ስለጉዳዩ የነገርኩት ነገር አልነበረም፡፡ ኋላ ነገሩን በዜና ሲሰማ በጣም ነው የወቀሰኝ፡፡ እንደሰማሁት ከሆነ ከዚያ በኋላ እንቅልፍ የለውም፡፡ “የልጄን መርዶ ከዛሬ ነገ ይነግሩኛል” እያለ ራሱን ለጭንቀት ዳርጓል፡፡

የህወሀት ጭካኔ ታጋይ ሆኖ ያውቀዋል። በጭለማ ዋሻ ውስጥ እንዳይሞት ትንሽ የሚቀመስ ምግብ እየሰጡ እኛን “ሳታስፈቅድ ወደ ቤተሰብህ ሄድክ” ብለው አስሮውት ከሞት በተአምር ያመለጠበትን አጋጣሚ ምንም ዘመኑ ቢረዝም አይረሳውም፡፡ ዛሬ ለእኔም ትውልድ ደርሰው እነዚህ ሰዎች በልጁ ህይወት ላይ መፍረድ የሚችሉ መሆናቸውን ሲያስብ እኔ የተቃዋሚ ፓርቲ አባል የሆንኩበትን ቀን እየረገመ መኖር እጣ ክፍሉ ሆኗል፡፡
ወደ ጉዳዩ ልመለስና የአረጋዊ ነገር እርግጥ ሆኖ እርማችን አወጣን፡፡ በብዙ አባሎቻችን ዘንድ ቁጣና እልህ ጎልቶ ይታይ ነበር፡፡ “እናንተ ናችሁ ህግ አለ.. ምንትስ እያላችሁ የምታስገድሉን ያላችሁት” ያሉኝ አባላት ነበሩ፡፡ በአንዳንዶቹ ላይ ደግሞ ፍፁም ተስፋ መቁረጥ ይታይ ነበር፡፡ ወዲያው አባሎቻችንን የማረጋጋትና የማጠናከር ስራ ባንሰራ ኖሮ ሁኔታዎች እጅግ በጣም አስቸጋሪ ይሆኑ ነበር፡፡ መቼም የአረጋዊ ሞት የእያንዳንዳችን የግል ህይወት በእጅጉ የነካ ጉዳይ ሆኖ ነው ያለፈው፡፡

አሁን ዙረያ ጥምጥሙን መጓዝ ትቼ ወደ ጉዳዩ በቀጥታ ልግባና የአረጋዊን አሟሟት በተመለከተ ታላቅ ወንድሙ አቶ አለም ገብረዮሐንስ ካሰፈሩት ፅሁፍ እነሳለሁ፡፡ ይህን የምልበት ምክንያት ፅሁፉ ሁሉም የሚያውቀውና ለሚመለከታቸው የመንግስት አካላት ሳይቀር እንዲደርሳቸው ተደርጎ በሰነድነት የተያዘ በመሆኑ ነው፡፡

“የወረዳው መርማሪ ፖሊስና አቃቤ ሕግ ግድያው “በመጠጥ ቤት ሂሳብ ክፈል አትክፈል” በሚል የተነሳ ተራ ጠብ ምክንያት የተፈፀመ በማስመሰል ሌሎች ተባባሪዎችን ወደ ጎን በመተው በቀጥታ በጩቤ ወግቶ የገደለውን ግለሰብ ላይ ብቻ ማትኮሩ አግባብነት የሌለው ነው፡፡ በሟች ቤተሰብ እምነት ምንም እንኳ በቀጥታ ወንጀሉን የፈፀመው በጩቤ የወጋው ግለሰብ ቢሆንም የግድያው አፈፃፀምና ዓላማ ግን በመጠጥ ቤት በተነሳ የሂሳብ ንትርክ የተፈጠረ ሳይሆን ሌላ መነሻ ያለው ነው የሚል ነው፡፡” ይህም በየካቲት 22/2002 ዓ.ም ማታ ስድስት ሰዓት አከባቢ መብራህቶም ጉዕሽ የተባለው ግለሰብ ወደ ሟች መጠጥ ቤት ገብቶ ትንሽ ቁጭ ካለ ኋላ ምንም ነገር ሳያዝ ተመልሶ ወጥቶ ሄዷል፡፡ ትንሽ ቆይቶ ግን ገዳዩን ፅጌ ብርሃነ እና ክብሮም ገብሩ የተባሉ ግለሰቦች መጥተው ቁጭ አሉ፡፡

በመጀመሪያ ወጥቶ የሄደው ሙብራህቶም ጉዕሽና ምላው በየነ ገብተው ከእነዚያ ራቅ ብለው እንደማይተዋቁ ሆነው ተቀመጡ፡፡ እንደገና ትንሽ ቆይቶ ተከሌ ማዕሾ የተባለ ሌላው ተባባሪ መጥቶ ለብቻው ተቀመጠ፡፡

ከዚያ አምስቱም ቦታ ቦታቸውን ይዘው እየጠጡ ሳለ ሚች መጥቶ "ጊዜው በጣም ስለመሸ የያዛችሁትን መጠጥ ጨርሳችሁ ወደ ቤታችሁ ሂዱ እኛም መተኛት እንፈልጋለን" ሲላቸው እነርሱ መጠጣት እንደሚፈልጉ ስለገለፁለት ጄኔሬተሩን አጥፍቶ በምትኩ ሻማ አብርቶላቸው ለሰራተኛዋ አስረክቧቸው ወደ መኝታው ሄደ፡፡ከዚያ ኋላ ሁሉም ወደ አንድ ጠረጴዛ ተሰባሰቡና ቁማር መጫወት ይጀምራሉ፡፡ ከሌሊቱ 8 ሰዓት አከባቢ እርስ በርስ የተጣሉ በማስመሰል የቢራ ጠርሙሶችን ወደ መሬት መከስከስ ይጀምራሉ፡፡ በዚህ ጊዜ ሚች የጭሆት ድምፅ ሰምቶ ወደ ቡና ቤቱ ተመልሶ ይገባል "ምንድነው የተፈጠረው" ብሎ ሳይጨርስ ፅጌ ብርሃኔ የተባለው ግለሰብ በጩቤ ሆዱን ወጋው፡፡ እንደገና ማጅራቱ ላይ ደገመው፡፡ ሚች ወደ መሬት ሲወድቅ ከኋላ እንደገና በመዞር ትልቁን የእግሩን የደም ስር በያዘው ጩቤ ቆረጠው፡፡ ይህ ሁሉ ሲሆን እዚያ የነበሩት ሌሎች ቆመው ግድያው በተሳካ ሁኔታ መካሄዱን ይመለከቱ ነበር፡፡ የሚረዳ ሌላ ሰው እንዳይመጣም ለመካላከል የተመደቡ ነበር የሚመስሉት፡፡ ጉዳዩን ያላወቀ አንድ የአከባቢው ምልሻ ጭሆት ሰምቶ ወደ ዚያ እያመራ ሳለ አንዱን ተባባሪ መንገድ ላይ አግኝቶት ነበር፡፡ "ምንድነው ጭሆት የምሰማው?" ብሎ ሲጠይቀው "እኔ አላውቅም ወደ ቤቴ እየሄድኩ ነው፡፡" ይለዋል፡፡ ኋላ እሱም እንደነበረበት ሲያረጋግጥ ግን ተከታትሎ እሱም ከሌሎቹ ጋር ልይዘው ችሏል፡፡ ቀንደኛው ገዳይ ግን ህዝቡን ነው ሊያመልጥ ሲል ተባብሮ በነጋታው የያዘው፡፡

በግድያው የተሳተፉት ግለሰቦች ብዛት አምስት ቢሆኑም የወረዳ አስገደ ፅምብላ አቃቤ ሕግና መርማሪ ፖሊስ ግን ግድያው በቀጥታ በጩቤ ወግቶ የገደለውን ብቻ በመያዝ እነዚያ ደግሞ ምስክሮች እንዲሆኑ በማድርግ ጉዳዩን በቻለው አቅም ሁሉ ለማድበስበስ ብዙ ጥረት አድረጓል፡፡

ከዚህም በአሻገር መንግስት ጉዳዩ የግል ፀብ ለማስመሰል ከፍተኛ የፕሮፓጋንዳ ስራ ሰርቷል፡፡ ጉዳዩ በዳኛ ተይዞ እያለ የወረዳው አስተዳዳሪ ግድያው የግል ጠብ መሆኑን ሲገልጥ በሌላ በኩል ደግሞ አንዴ "በጠብ መካከል ሊገላግል ገብቶ ነው የተገደለው" ሲሉ ሌላ ጊዜ ደግሞ "በደንበኛው ነው የተገደለው" ሲሉ በዳኛው ውሳኔ ላይ ተፅዕኖ ሊፈጥሩ የሚችሉ የተለያዩ ሃሳቦችን በሚዲያዎቻቸው ሲያሰራጩ ነበር፡፡ ከሁሉም በላይ የሚገርመው ደግሞ የማስታወቂያ ሚኒስትሩ ለውጭ ሚዲያዎች የሰጡት መግለጫ ነው፡፡ አቶ በረከት ስምኦን "Aregawi was killed in bar fight" ነበር ያሉት፡፡ በአገራችን መዋሸት ነውር ነው፡፡ ባህላችንም አይደለም፡፡ አንድ ሰው ሚኒስተር ሆኖ ሲዋሽ መስማት ደግሞ ጦሱ ለእኛ ብቻ ሳይሆን ለአዲሶቹም ትውልዶች የሚተርፍ ነው፡፡ የሚዋሹ መሪዎች ያሉት ህዝብ ምን ዓይነት ትውልድ እንደሚያፈራ መገመት ይቻላል፡፡ በመሰረቱ አረጋዊ የተገደለው በራሱ ቤት ውስጥ ነው፡፡ እንደ አጋጣሚ ሆኖ እንዲያ ቢሆንስ "መጠጥ ቤት የተገኘ ይገደል" የሚል ሕግ የለም፡፡ እንደዚህ ዓይነት ክርክር የምናመጣ ከሆነ ደግሞ ጀግናው ሐየሎም አርአያም የተገደለው መጠጥ ቤት እንደነበር ሁላችንም የምንዘነጋው አይመስለኝም፡፡ ስለዚህ ዋናው ነጥብ መሆን ያለበት ግድያው ሆቴል ውስጥም ይፈፀም ቤተክርስቲያን ውስጥ የአፈፃፀሙ ሁኔታና ዓላማ ነው፡፡

ከዚህ አንፃር የአረጋዊ ጉዳይ ወደ አረጋዊ ግሮሰሪ ጩቤ ይዞ መግባቱ ግድያውን ለመፈፀም ሆን ብሎ ቀድሞ ተዘጋጅቶ መምጣቱን የሚያመላክት ነው፡፡ እንዲያውም ጩቤው በምን መልክ እንዳገኘውም ጭምጭታ እየተሰማ ነው፡፡
ሌላው ነጥብ ሌሎቹ ተባባሪዎች ሰው እንደ በግ ሲታረድ እያዩ ለመግታት ወይም ለመጮህ ምንም ዓይነት ጥረት ያለማድረጋቸው የሌሎችም እጅ እንዳለበት ሌላው ጥሩ አመላካች ነው፡፡

እንደገና የወረዳው ፍርድ ቤት ጉዳዩን በደንብ ሳያጣራ የሌላውን አፍ ለማዘጋት የተፈለገ በሚያስመስል መልኩ በፍጥነት ጉዳዩን በ15 ዓመት ሌሎቹ ተባባሪዎች ደግሞ በነፃ አሰናብቶ ምስክር እንዲሆኑ ማድረጉ ነው፡፡ ይህ ግድያ የህግ ባለሞያዎች እንደነገሩን ከሆነ የጭካኔ አገዳደል በመሆኑ ከፍ ሲል በሞት ዝቅ ስል ደግሞ በእድሜ ልክ እስራት ነው የሚያስቀጣው፡፡

አሁንም ቅድም የጠቀስኩት ተመሳሳይ ግድያ ለንፅፅር እንመልከት፡፡ የደህንነት ሐላፊው የአቶ ክንፈ ገብረመድህን ጉዳይ እና የሀየሎም ጉዳይ ሁለቱም በጥይት ነው ግድያውን የፈፀሙት ነገር ግን ሞት ነው የተፈረደባቸው፡፡ ስለዚህ በአሁኑ ጊዜ እዚህ አገር ሁለት ዓይነት ሕግ እንዳለ የሚያሳይ ነው፡፡ አንዱ ለገዥዎች የሚሰራ ሕግ ሲሆን ሌላው ደግመሞ ለተራው ዜጋ የሚሰራው ሕግ!

አንዲት ቀበጥ የድምፅ ወያኔ ጋዜጠኛ በዚህ ጉዳይ ላይ ጥያቄ ስታቀርብ "ጉዳዩ በሕግ ተዘግቶ እያለ እናንተ እንደዚህ ማለታችሁ በዳኝነቱ ስርዓት ላይ እምነት እንደሌላችሁ አያመላክትም ወይ?" ብላኝ ነበር ባለፈው የፕሬስ መግለጫ በሰጠንበት ጊዜ! የአረጋዊ ጉዳይ ገና ነው፡፡ ፍትሕ አላገኘም፡፡ እዚህ አገር ገለልተኛ የሆነ የዳኝነት ስርዓት እንደሌለ ምስክር መጥራት የሚያስፈልገው ጉዳይ አይደለም፡፡ ሕግ ቢኖርማ ወ/ት ብርትኳን ሚደቅሳ አሁን በእስር ቤት ባልተሰቃየች ነበር፡፡ ፍትሕ ቢኖርማ አቶ ስዬ ታግለው ባፀደቁት ሕገ መንግስት ላይ በግልፅ የተቀመጠውን ዋስ የማግኘት መብት ተነፍገው ለዓመታት በእስር ባልማቀቁ ነበር፡፡ ብዙ ብዙ ሌሎችም ዜጎች በምሳሌ ማምጣት ይቻላል፡፡ ስለዚህ የአረጋዊ ጉዳይ ገና ነው፡፡ ከእስር ዓመታትም በኋላ ተጠናክሮ የሚቀጥል ትክክለኛ ፍትሕ እስኪገኝ ድረስ የምንታገልለት አጀንዳ ነው እንጂ እንዲሁ በቀላሉ የምንተወው ነገር አይሆንም፡፡ አለበዚያማ የሁለቱ ጓኞሞቹ ታሪክ ነው የምንደግመው፡፡ አንድ የትግርኛ ተረት አለ፡፡ ሁለት ጓደኞሞች ወደ ሩቅ አገር በእግር ሲጓሱ መንገድ ለላይ ይመሽባቸውና በአንድ ዛፍ ስር ጎን ለጎን ይተኛሉ፡፡ ሌሊት አንደኛው የሆነ ነገር ሲያኝክ ይሰማና ጓደኛውን ይቀሰቅሰዋል፤ **"እረ የሆነ ድምፅ ይሰማኛል፡፡ ፈጥነን እንነሳ"** ይለዋል፡፡ ያኛው በሹኩሹኩታ **"ወንድሜ ዝም በል! እንዳታስጨርሰን! ጅብ እግሬን እየበላኝ ነው፡፡"** አለው ይባላል፡፡ ከእግር መበላት ወዲያ ዝም ማለት የት አለ! ቢያንስ ለሌላው ምሳሌ በሚሆን መልኩ እየጮሁም፣ እየታገሉም መበላት ይሻላል እንጂ!